- እግዚአብሔር ለአብራም ቃል ከገባ በኋላ አብራም ምን አደረገ?

ዘፍጥረት 12፡4-5

4- ስለዚህ አብራም እግዚአብሔር እንዳዘዘው ወጣ፤ ሎጥም አብሮት ሄደ። አብራም ከካራን ሲወጣ፣ ዕድሜው 75 ዓመት ነበር።

5- አብራምም ሚስቱን ሦራንና የወንድሙን ልጅ ሎጥን አስከትሎ፣ በካራን ሳሉ ያፈሩትን ሀብትና የነበራቸውን አገልጋዮች ይዘው በመጓዝ ከነዓን ምድር ገቡ።

- አብራም ይኖርበት የነበረውን አገር ለቅቆ እግዚአብሔርን በመከተል እርሱ ወደሚመራው አገር ሄደ።

- እግዚአብሔር አብራምን የመራው ወዴት ነበር?

- እግዚአብሔር አብራምን ከነዓን ወደሚባል አዲስ አገር መራው።

- በሚቀጥለው ትምህርት በከነዓን ምድር በአብራም ላይ ምን እንደደረሰበት እንማራለን።



## ትምህርት 19

1. ከኖኅ በኋላ የተወለዱት ሰዎች እነማን ነበሩ?

ሀ- የእኔና የእናንተ የቀድሞ አባቶች ነበሩ።

2. የቀድሞ አባቶቻችን ስለእግዚአብሔር ያውቁ ነበር?

ሀ- አዎን።

3. የቀድሞ አባቶቻችን ስለእግዚአብሔር ሊያውቁ የቻሉት እንዴት ነው?

ሀ- በመጀመሪያ ደረጃ የቀድሞ አባቶቻችን ስለ እግዚአብሔር ያወቁት፤ ከእነርሱ በፊት የነበሩት ሽማግሌዎች ስለ እግዚአብሔርና ስለ ጥፋት ውኃ ስለ ነገሯቸው ነበር።

4. ሽማግሌዎች ለወጣቶቹ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ጥፋት ውኃ የነገሯቸው ምን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደሚጠላ ከዚህ የተነሣም ኖኅና ቤተሰቡን ብቻ አስቀርቶ ሌሎችን ሰዎች ሁሉ እንዳጠፋ ነው የነገሯቸው።

5. ከዚህ ሌላ የቀድሞ አባቶቻችን ስለእግዚአብሔር ሊያውቁ የቻሉት እንዴት ነው?

ሀ- በሁለተኛ ደረጃ ቀስተ ደመናው ስለ እግዚአብሔር ስለነገራቸው ነው።

6. ቀስተ ደመናው ለቀድሞ አባቶቻችን ስለ እግዚአብሔር ምን ነገራቸው?

ሀ- እግዚአብሔር ሰዎችን እንደሚወድድና ምድርን ዳግመኛ በጥፋት ውኃ እንደማያጠፋት።

7. አሁንም ከዚህ ሌላ፥ የቀድሞ አባቶቻችን ስለእግዚአብሔር ሊያውቁ የቻሉት እንዴት ነው?

ሀ- በሦስተኛ ደረጃ አባቶቻችን ስለ እግዚአብሔር ያወቁት ሰማይ ተራሮች ወንዞችና ዛፎች ስለ እግዚአብሔር ስለ ነገሯቸው ነው።

8. ሰማይ ተራሮች ወንዞችና ዛፎች ስለ እግዚአብሔር ምን ነገሯቸው?

ሀ- እግዚአብሔር ብቻ አምላክ መሆኑን ሰዎችም እርሱን ብቻ መከተል እንደሚገባቸው ነገሯቸው።

9. ስለ እግዚአብሔር ቢያውቁም ከቀድሞ አባቶቻችን ብዙዎች በእግዚአብሔር ያምኑ ነበር?

ሀ- አልነበረም።

ለ- ከቀድሞ አባቶቻችን መካከል በእግዚአብሔር ያመኑት ጥቂቶቹ ብቻ ነበሩ።

10. ከቀድሞ አባቶቻችን ብዙዎቹ እግዚአብሔርን ከመከተል ይልቅ የተከተሉት ማንን ነበር?

ሀ- አብዛኛዎቹ የቀድሞ አባቶቻችን የተከተሉት ሰይጣንንና የእርሱን የውሸት ሃሳብ ነበር።

11. ሰይጣን አባቶቻችን ምን እንዲያደርጉ ነበር የነገራቸው?

ሀ- ለፀሐይ ለጨረቃና ለክዋክብት መስዋዕት እንዲያቀርቡ።

ለ- ለዛፎች ለወንዞችና ለሙታን መናፍስት መስዋዕት እንዲያቀርቡ።

ሐ- እንጨትና ድንጋይ በሰውና በእንስሳት መልክ በመቅረጽ ለእነርሱ መስዋዕት እንዲያቀርቡ።

12. እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ በአንድ ላይ በአንድ ስፍራ እንዲኖሩ ያልፈለገው ለምን ነበር?

ሀ- ሰዎች እግዚአብሔርን እንዳይረሱትና ኃጢአታቸው ብዙ እንዳይሆን።

13. ሰዎች በባቤል ረጅም ግንብ መገንባት ለምን ፈለጉ?

ሀ- ሰዎቹ እጅግ ስለ ታበዩ።

ለ- ሰዎቹ የራሳቸውን ስም ማስጠራት ስለ ፈለጉ።

14. ሰዎች ረጅም ግንብ መሥራት መጀመራቸውን እግዚአብሔር አይቷል?

ሀ- አዎን።



- አራተኛ እግዚአብሔር ከአብራም ዘር በሆነ በአንድ ሰው አማካይነት ሰውን ሁሉ እንደሚባርክ ቃል ገባ።

- እግዚአብሔር ከአብራም ዘር በሆነው አንድ ሰው ሁሉንም ሰው እንደሚባርክ የገባው ቃል፥ ከሁሉም የሚበልጥ የተስፋ ቃል ነው።

- ከአብራም ዘር የሆነውና ሰዎች ሁሉ በእርሱ አማካይነት የሚባረኩበት ማን ነው?

- አዳኙ።

- አዳኙ የሚመጣው ምን ለማድረግ ነው?

- አዳኙ የሚመጣው የኃጢአትን ኃይል ለማሸነፍ ነው።

- አዳኙ የሚመጣው የሞትን ኃይል ለማሸነፍ ነው።

- አዳኙ የሚመጣው የሰይጣንን ኃይል ለማሸነፍ ነው።

- አዳኙ የሚመጣው እግዚአብሔርና ሰው ዳግመኛ ኅብረትን እንዲያደርጉ ለማስቻል ነው።

- አዳኙ ሰይጣንን ያሸንፋል በዓለም ላይ የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ይባርካል።

- አብራም በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ያምን ነበር?

- አዎን።

- አብራም እግዚአብሔር እንደማይዋሽ አመነ።

- አብራም እግዚአብሔር እውነትን ብቻ እንደሚናገር አመነ።

2- «ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ። ደግሞም እባርክሃለሁ። ስምህን ገናና አደርገዋለሁ፤ ለሌሎች በረከት ትሆናለህ።»

- እግዚአብሔር ለአብራም የገባለት የተስፋ ቃል ምን ነበር?

- አንደኛ እግዚአብሔር አብራም ታላቅ ሕዝብ የሚሆኑ ብዙ ዘሮች እንደሚኖሩት ቃል ገባ።

- በዚያን ጊዜ አብራምና ሦራ ስንት ልጆች ነበሯቸው?
- ምንም ልጅ አልነበራቸውም።

- አብራምና ሦራ ምንም ልጅ ያልነበሯቸው ለምንድን ነው?
- የአብራም ሚስት ሦራ መካን ስለ ነበረች ነው።

- አብራም ምንም ልጅ ባይኖረውም ብዙ ልጆችን እንደሚሰጠው እግዚአብሔር ለአብራም ቃል ገባለት።

- ሁለተኛ እግዚአብሔር አብራምን እንደሚባርከው ቃል ገባ።

- እግዚአብሔር ለአብራም የገባለትን የተስፋ ቃል ጨምረን እናንብብ፡-

ዘፍጥረት 12፡3

3- «የሚባርኩህን እባርካለሁ፤ የሚረግሙህን እረግማለሁ በምድር የሚኖሩ ሕዝቦች በአንተ አማካይነት ይባረካሉ።»

- ሦስተኛ እግዚአብሔር አብራምን የሚባርኩትን እንደሚባርክ የሚረግሙትን እንደሚረግም ቃል ገባ።



15. እግዚአብሔር የሁሉንም ሰው አስተሳሰብ ያውቃል?
ሀ- አዎን።
ለ- አንድ ሰው ስለ አንድ ነገር ከማሰቡ አስቀድሞ እግዚአብሔር የሰውየውን አሳብ ሙሉ በሙሉ ያውቃል።

16. እግዚአብሔር ሰዎች የሚናገሩትን ሁሉ ያውቃል?
ሀ- አዎን።
ለ- አንድ ሰው አንድ ነገር ከመናገሩ በፊት እግዚአብሔር ሰውየው የሚናገረውን ቃላት ሙሉ በሙሉ ያውቃል።

17. እግዚአብሔር የሁሉንም ሰዎች ሥራ ያውቃል?
ሀ- አዎን።
ለ- አንድ ሰው አንድን ሥራ ከመጀመሩ በፊት እንኳ እግዚአብሔር ሰውየው ምን ሊያደርግ እንደ ሆነ ሁሉንም ነገር ሙሉ በሙሉ ያውቃል።

18. እግዚአብሔር ሰዎችን ይረሳል?
ሀ- እግዚአብሔር ሰዎች የሚያስቡትን ፈጽሞ አይረሳም።
ለ- እግዚአብሔር ሰዎች የሚናገሩትን ፈጽሞ አይረሳም።
ሐ- እግዚአብሔር ሰዎች የሚያደርጉትን ፈጽሞ አይረሳም።

19. የቀድሞ አባቶቻችን ለእግዚአብሔር ስላልታዘዙ እግዚአብሔር ሊቀጣቸው ወሰነ። እግዚአብሔር ሊቀጣቸው የወሰነው በምን ነበር?
ሀ- እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ቋንቋን ሰጣቸው። ከዚህ የተነሣም አንዱ ከአንዱ ጋር መግባባት አልቻለም።

20. እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው ልዩ ልዩ ቋንቋን ከሰጠ በኋላ ሌላስ ምን አደረገ?
ሀ- እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው በምድር ላይ ወዳሉ ልዩ ልዩ ቦታዎች በተናቸው?

21. አባቶቻችሁ በመጨረሻ አሁን ወዳላችሁበት ስፍራ የመጡት እንዴት ነበር?

ሀ- ከብዙ ብዙ ዓመታት በኋላ በእግራቸውና በጀልባ ተጉዘው ነው እዚህ የመጡት።

- ከኖኅ በኋላ የኖሩት የቀድሞ አባቶቻችን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ባለመስማት የባቤልን ረጅም ግንብ መሥራት ጀመሩ።

- እነርሱ ሰይጣን የተናገረውን ውሸት ተከተሉ እንጂ እግዚአብሔር የተናገረውን እውነት አልተከተሉም።

- እነርሱ እግዚአብሔርን ትተው የራሳቸውን መንገድ ተከተሉ።

- የቀድሞ አባቶቻችን እግዚአብሔርን ስለተዉ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማዳን ያቀደውን ዕቅድ ትቷል?

- አልተወም።

- የቀድሞ አባቶቻችን እግዚአብሔርን ስለተዉ፥ እግዚአብሔር አዳኝ የመላኩን ዕቅድ ትቷል?

- አልተወም።

- እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ቃል ከገባ ሁልጊዜም ቃሉን ይጠብቃል።

- እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ በኤድን የአትክልት ስፍራ ለአዳምና ለሔዋን ቃል ገባ።

- እግዚአብሔር ቃሉን አያጥፍም።



- የዑር ሕዝብ ሰይጣንና የእርሱን ውሸተኛ ነገር ስለሚከተል ነው።

- እግዚአብሔር በእርሱ የሚያምኑ ሰዎችን ለራሱ ለመለየት ስለ ፈለገ ነው።

- እግዚአብሔር ለአብራም የተናገረው እንዴት ነበር?

- እግዚአብሔር ለአብራም የተናገረው በድምፅ ነበር።

- እግዚአብሔር ለአብራም በድምፅ የተናገረው አብርሃም በኖረበት ዘመን የእግዚአብሔር መጽሐፍ ገና ስላልተጻፈ ነበር።

- እግዚአብሔር ዛሬ ለእኛ የሚናገረው እንዴት ነው?

- ዛሬ በአብዛኛው እግዚአብሔር በድምፅ አይናገረንም።

- ዛሬ በአብዛኛው እግዚአብሔር የሚናገረን በመጽሐፉ በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ነው።

- የእግዚአብሔርን ቃል የምንሰማው መጽሐፉን በማንበብ ነው።

- እግዚአብሔር በመጽሐፉ ውስጥ የጻፈውን በማንበብ፥ እግዚአብሔር የሚናገረንን እናውቃለን።

- እግዚአብሔር ለአብራም በተናገረበት ጊዜ የተስፋው ቃል ገብቶለት ነበር።

- እግዚአብሔር ለአብራም የገባው የተስፋው ቃል ይህ ነው፡

ዘፍጥረት 12፡2

- ሦራ መካን ስለ ነበረች።

- አብራምና ሦራ በዑር ከተማ ይኖሩ ነበር።

- የዑር ሰዎች በእግዚአብሔርና እግዚአብሔር በተናገራቸው እውነተኛ ነገር አያምኑም ነበር።

- የዑር ሕዝብ ሰይጣንና የእርሱን ውሸተኛ ነገር ተከተለ።

- የዑር ሕዝብ ክፉ ሕዝብ ነበር።

- አብራም በዑር ሲኖር ሳለ እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠለት።

- እግዚአብሔር ለአብራም ያለው ይህን ነበር-፡

ዘፍጥረት 12፡1

1- እግዚአብሔር ለአብራም እንዲህ አለው፤ «አገርህን፣ ወገንህንና የአባቶችህን ቤት ትተህ እኔ ወደ ማሳይህ ምድር ሂድ።»

- እግዚአብሔር አብራም ምን እንዲያደርግ ነገረው?

- እግዚአብሔር አብራም አገሩን ለቅቆ እርሱ ወደሚያሳየው አገር እንዲሄድ የነገረው።

- እግዚአብሔር አብራም አገሩን ዑርን ለቅቆ እንዲሄድ የነገረው፥ ለምንድን ነው?

- የዑር ሰዎች በእግዚአብሔርና እግዚአብሔር በተናገራቸው እውነተኛ ነገር የማያምኑ ስለሆኑ ነው።



- እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ ለሴት ለሔኖክና ለኖኅ ቃል ገባላቸው።

- እግዚአብሔር ቃሉን አያጥፍም።

- የቀድሞ አባቶቻችን እግዚአብሔርን ቢተውም እንኳ እግዚአብሔር አዳኝ ለመላክ ያቀደውን ዕቅድ አልተወም።

- የቀድሞ አባቶቻችን እግዚአብሔርን ቢተውም እንኳ እግዚአብሔር ሰዎችን ከኃጢአታቸው ለማዳን አዳኝ መላክ ፈልጓል።

- የቀድሞ አባቶቻችን እግዚአብሔርን ቢተውም እንኳ እግዚአብሔር ሰዎችን ከሞት ለማዳን አዳኝ መላክ ፈልጓል።

- የቀድሞ አባቶቻችን እግዚአብሔርን ቢተውም እንኳ እግዚአብሔር ሰዎችን ከሰይጣን ለማዳን አዳኝ መላክ ፈልጓል።

- ሰዎች እግዚአብሔር አዳኝ እንዳይልክ መከልከል ይችላሉ?
- አይችሉም።

- አጋንንት እግዚአብሔር አዳኝ እንዳይልክ መከልከል ይችላሉ?

- አይችሉም።

- ሰይጣን እግዚአብሔር አዳኝ እንዳይልክ መከልከል ይችላል?
- አይችልም።

- እግዚአብሔር አዳኝ እንዳይልክ መከልከል የሚችል ማን ነው?
- ማንም የለም።

- እግዚአብሔር አዳኝ ለመላክ ሲወስን ማንም መከልከል አይችልም።

- አብዛኛዎቹ የቀድሞ አባቶቻችን እግዚአብሔርን ስላልፈለጉ እግዚአብሔር አዳኝ ከዘሩ የሚመጣበትን አንድ ሰው ለመምረጥ ወሰነ።

- እግዚአብሔር የመረጠው ሰው አብራም ይባላል።

- እግዚአብሔር ከአብራም ዘር አዳኝ እንዲመጣ መረጠ።
- እግዚአብሔር ከአብራም ዘር አዳኝ ለመላክ የወሰነው ለምንድን ነው?

- እግዚአብሔር አብራምን የመረጠው አብራም ኃጢአት ስላልሠራ ነበር?
- አልነበረም።

- አብራም ኃጢአተኛ ነበር።

- አብራም የአዳም ዘር ነበር።
- አብራም ኃጢአተኛ ሆኖ ነበር የተወለደው።

- እግዚአብሔር አብራምን ለምን መረጠው?

- አብራም እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን ስላመነ።
- አብራም ኃጢአተኛ መሆኑን ስላመነ።

- አብራም ለኃጢአቱ የሚገባው ቅጣት ሞት እንደሆነ ስላመነ።

- አብራም ከኃጢአቱ ሊያድነው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ስላመነ።

- አብራም እግዚአብሔር አዳኝ እንደሚልክ ስላመነ።



- አብራም በእግዚአብሔር ያምን ስለ ነበር እግዚአብሔር ከእርሱ ዘር አዳኝ ለመላክ መረጠ።

- የአብራም አባት ታራ ነበር።
- ታራ የሴም ዘር ነበር።

- የኖኅን ልጆች ስም ታስታውሳላችሁ?
- ሴም ካምና ያፌት ናቸው።

- አብራም ከኖኅ ልጆቹ አንዱ የሆነው የሴም ዘር ነበር።

ዘፍጥረት 11፡27 & 29-30

27- የታራ ትውልድ ይህ ነው። ታራ፣ አብራምን ናኮርንና ሐራንን ወለደ፤ ሐራንም ሎጥን ወለደ።

29- አብራምና ናኮር ሁለቱም ሚስት አገቡ፤ የአብራም ሚስት ሦራ ስትባል፣ የናኮር ሚስት ደግሞ ሚልካ ትባል ነበረች። ሚልካም የሐራን ልጅ ናት፤ ሐራንም የሚልካና የየስካ አባት ነበረ።

30- ሦራ መካን ነበረች፤ ልጅም አልነበራትም።

- አንድ ቀን አብራም ሚስት አገባ።

- አብራም ሦራ የተባለች ሴት አገባ።

- ይሁን እንጂ አብራምና ሦራ ልጆች አልነበሯቸውም።

- አብራምና ሦራ ልጅ ያልወለዱት ለምንድን ነው?